# ★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞክራሲያ ቅጽ** 36 **ቁጥር** 6 **መጋቢት** 2003 **ዓ.ም**

## *የጭቆና ገመድ ሲበጠስ፣ ሕዝባዊ አመፅ ሲቀሰቀስ*

*የሰው ልጅ የሚኖርባት ይህች ዓለም በቅራኔዎች የተመላች በመሆኗ፣ የቅራኔዎቹ መፈራረቅና መለዋወጥ፣ ለኅልውናዋ ማረጋገጫ ሆነው ይኖራሉ። እርሷም በቅራኔዎቹ ሂደት ውስጥ የራሷን ሂደት እያካሄደች ብርሃን ለጨለማ፣ ሠላም ለጦርነት፣ ደስታ ለሀዘን፣ ምቾት ለእንግልት፣ ነፃነት ለባርነት፣ ጥጋብ ለረሀብ፣ ፍትኅ-ርትዕ ለበደል፣ ሀሴት ለመከራ፣...ወዘተ ተራቸውን እየለቀቁ፣ ለሰው ልጅ ሰቆቃና ችግር ምክንያት በመሆን እስካለንበት ምዕተ-ዓመት ደረስ ቆይተዋል።*

*የወደፊቱን መተንበይ ባይቻልም የሰው ልጅ መከራና ስቃይ እየተባባሰ እንዳይቀጥል ለብሩኅ ተስፋና ለምልዓተ ሕዝብ ሠላምና ብልፅግና እየቆሙ መታገል ግድ ይሆናል። የብርሃንና ጨለማ መፈራረቅ ለህይወት ጠቃሚ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም በጨቋኝና በተጨቋኝ፣ በገዥና በተገዥ፣ መካከል ያለው ቅራኔ ግን በውድም ይሁን በግድ መወገድ አለበት። ያ ካልተወገደ በዓለም ውስጥ መረጋጋትና ሠላም አይገኝም። በጨቋኝና በተጨቋኝ፣ በገዥና በተገዥ መካከል ያለው ቅራኔ ካልጠፋ ገዥዎች እየገዙ፣ ተገዥዎች እየተገዙ ለብዙ ጊዜ አብረው ለመኖር አይችሉም። አጥፊና ጠፊዎች በመሆናቸው ተስማምተው መኖር አይሆንላቸውም። የአንዱ መጥፋት ለሌላው ሕይወት በመሆኑ፣ ተጨቋኞቹ ባለመብት ሁነው በሰላምና በብልፅግና ለመኖር ከፈለጉ፣ ጨቋኞቻቸውን ማስወገድ አለባቸው። የጭቆናው ሰንሰለት ሲበጣጠስ ደግሞ፣ ነፃነትና ፍትኅ የሚሰፍንበት ሁኔታ መፈጠሩ አይቀርም። ይኸም፣ ሰሞኑን በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ እየተካሄደ ያለው ክስተት ህያው ምስክር ነው።*

*ይህ በአካባቢያችን እየተካሄደ ያለው የሕዝብ አመፅ ወላፈን፣ ወያኔንና የበላይ ጠባቂዎቹን ያስጨነቃቸውና እንቅልፍ ያሳጣቸው መሆኑ ከሚያደርጉት መቅበዝበዝ መገንዘብ ይቻላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በደሉና ብሶቱ ከመጠን ስላለፈ ለአለፉት ሃያ የመከራ፣ የውርደት፣ የጥቃትና የሀፍረት ዘመን፣ በሀገራችን ላይ የወረደውን መቅሰፍት በሕዝባዊ አመጽ አሽቀንጥሮ የሚጥልበት ሁኔታ ጎላ ብሎ ይታያል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ፣ ምሥጢርክን በጉያ ስንቅህን በአህያ ብሎ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል። የቁርጧ ቀን እውን ስትሆን፣ ሕዝባዊ አመጽ ሲከሰት ወያኔና አጫፋሪዎቹ የሚያድናቸው የውጭ ኃይል እንደማይኖር፣ በቱኒዚያና በግብፅ የታየው ክስተት አረጋግጧል። መጀመሪያ ወዳጆቻቸውን ለማዳን ቢጥሩም የኋላ ኋላ የበሰበሰውን ጨቋኝ ሥርዓት እየገረሰሰ ከነበረው አዲስ ኃይል ጋር ሰልፋቸውን ሲያሳምሩ ታዩ እንጅ፣ በከርሰ-መቃብር ላይ ሆኖ የሚጠራሞተውን አሮጌ ፈረስ ለማዳን ጊዜያቸውን ሲያጠፉ አልታዩም። ወረተኛን፣ ወረቱ ካለፈ ዘወር ብሎ ማንም እንደማያየው የዓለም ታሪክ ያረጋገጠው ሐቅ ነው። ዛሬ፦*

*"ወያኔ ይነግድ እኛስ አንነግድም፣*
*ወረቱ ካለቀ እርሱ አይወደድም "*

*እየተባለ የሚዘፈንበትም እኮ በዚህ ምክንያት ነው።*

*የወያኔ ሥርዓት አራማጆች ባሁኑ ወቅት ከሚያንዣብበው ሕዝባዊ አመፅ ለመከላከል ይጠቅመን ይሆናል የሚሉትን ሁሉ እያደረጉ ናቸው። ወታደሮችንና የፀጥታ ኃይሎችን በቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች በማሰማራት፣ በየቀበሌው ወላጆችን ልጆቻቸሁን ጠብቁ የሚል የፍርሃት ፕሮፓጋንዳ በማሰራጨት፣ በቡድኑ መገናኛ ብዙሃን በሰሜን አፍሪካና በአንዳንድ የአረብ አገሮች እየተካሄዱ ያሉት ሕዝባዊ አመጾች እንዳይተላለፉ በመከልከል፣ በሌሎች ክፍሎች የሚካሄዱ የዜና ማሰራጫዎች ሞገዶችን የፍኖተ ዴሞክራሲ ሬዲዮን ጨምሮ በማፈን (ጃም በማድረግ)፣ ...ወዘተ ሕዝባዊ አመጽ በአገራችን እንዳይከሰት የቻሉትን መከላከያ እየፈጠሩ ነው። በተጨማሪም*

በዘረኝነት ላይ የተመሠረተው የጎሳ መጫወቻ ዘዴያቸው ተሚጥጦ ቢያልቅባቸውም፣ የውሸትና የማታለል ቋታቸው ግን ገና ተጨልፎ ባዶ አልሆነም። የወያኔው መሪ ሰሞኑን የሚያደርገው ለከት የለሽ ማጭበርበር፣ አሰፍስፎ የመጣውን የሕዝብ አመፅ አቅጣጫ ለመለወጥና ትኩረቱንም ለማደብዘዝ ይጠቅመኛል ብሎ ይገምታል። ለዚህም ጥረቱ፣ የለመደበትን የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በሰፊው ተያይዞታል። ሰሞኑን በብቸኝነት የሚቆጣጠረውን የግል መገናኛ ብዙኃንን እየተጠቀመ፣ የነፍስ-አድን ጥረት በማድረግ የታሪክን ሂደት ለመቀልበስ በመፍጨርጨር ላይ ነው። ገንፍሎ የሚመጣን ሕዝባዊ አመፅ፣ በአራዳ ጮሌነትና በመገናኛ ብዙኃን በሚለፈፍ ጥሩንባ መግታት የሚቻል ይመስል፣ ግብረ-አበሮቹ እንዳይጨነቁ፣ "አይዟችሁ ተረጋጉ !" የሚል የማጽናኛ መልዕክት አስተላልፏል። ለዚህ የማጽናኛ መልዕክት ይጠቅማኛል ብሎ በመረጣቸው አምስት ነጥቦች ዙሪያ እየተሽከረከረ የኢትዮጵያን ሕዝብ የአመጽ አቅጣጫና ትኩረት ለመስለብ ጥረት አድርጓል። እነኝህን ነጥቦች መምረጡ፣ በሌሎች ሀገሮች የተነሳው ሕዝባዊ አመፅ በጭራሽ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊመጣ አይችልም ሊል የሚሞክረውን ማጠየቂያ ያገኘ መስሎት ለመሆኑ፣ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰወረ ሊሆን አይችልም። አምስቱም ያነሳቸው ነጥቦች፣ እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ በመሆናቸው ምክንያት፣ ያተኮሩበትን ዒላማ ሊመቱ አልተቻላቸውም። የወያኔው መሪ፣ የሚከተሉትን አምስት ነጥቦች አንስቶ፣ እነኝህ ነጥቦች እያሉ፣ ሕዝባዊ አመፅ በኢትዮጵያ ሊመጣ አይችልም ሲል ደምድሟል።

1ኛ. እኛ የተመረጥነው 99. 6 ከመቶ ደምፅ አግኝተን በመሆኑ፣
2ኛ. ለመጭው አምስት ዓመታት ውል/ኮንትራት ስለፈረምን፣
3ኛ. የእኛ ሕገ መንግሥት ሕዝባዊ አመፅ እንዳይደረግ ስለሚከለክል፣
4ኛ. ሕዝብ ቅሬታውን ለማሰማት ግልፅና ነፃ መድረክ መጠቀም ስለሚችል፣
5ኛ. የፈረምነውን ውል/ኮንትራት ለመፈፀም ተግተን ስለምንሰራ፣

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝባዊ አመፅ ፈፅሞ ሊነሳ አይችልም ብሎ ደምድሟል።

ኧረ ለመሆኑ ከመቸ ወዲህነው ሕዝባዊ አመፅ የአምባገነኖችን ፈቃድና ስምምነት አግኝቶ የሚመጣው? የትኛው አምባገነን ነው ሕዝብን፣ እባክህ፣ ተነስተህ አምፅና ከሥልጣኔ አውርደህ ገላግለኝ ብሎ ፈቃድ የሚሰጠው? ወያኔ፣ ሕገ መንግሥት የሚለው፣ የማንን ሕገ መንግሥት ነው? የምን ሕገ መንግሥት ነው? የአንድ ጠባብ ብሔር የፖለቲካ መርህ ግብር፣ ለኅብረ-ብሔራዊት ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ሊሆን እንደማይችል ለአለፉት ሃያ ዓመታት በማያሻማ መልኩ ተረጋግጧል። በማንኛውም መስፈርት ቢለካ፣ የዕርሱ የራሱ ባልሆነ "ሕገ መንግሥት" ሊገዛና ሊታዘዝ፣ ብሎም ለማመፅ ፈቃድ የሚጠይቅ ሕዝብ ሊኖር አይችልም። የኢትዮጵያ ሕዝብም ቢሆን፣ ከዚህ የዓለም አቀፍ ክስተት ውጭ እንዲያስብ አይጠበቅበትም። "አምባገነን ገዥ ያስገብራል የትም፣ ሥልጣንም የሰው ነች ለማንም አይሰጥም " ለሚለው የትዕቢት አዋጅ፣

"አመፅ የሕዝብ ነው ፈቃድ አይጠይቅም፣
ድሉን ይቀዳጃል መሥዋዕት ቢከፍልም"

የሚል ምላሽ እየሰጠ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማመፁን ይቀጥልበታል ።

የወያኔ ባለሥልጣኖች፣ ማንም ተወዳዳሪ ባልነበረበት ሜዳ እራሳቸው በብቸኝነት ሮጠው ራሳቸውን በማቸነፍ የራሳቸውን የምርጫ ሳጥን ከፍተው በቆጠሩት 99 ነጥብ 6 ከመቶ ድምፅ አግኝተንበታልና የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአመፅ ሊነሳ አይችልም የሚለው አስተሳሰብ፣ ዶሮ ጭራ ከምታወጣው ጥሬ የበለጠ ክብደት አይኖረውም። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ ሊያነሳ አይችልም የሚለው የወያኔ ዝባዝንኬ፣ ደጋፊዎችንና የበላይ ጠባቂዎችን ጊዜያዊ እፎይታ ከመስጠት ያለፈ እርባና ሊያመጣ አይችልም። የኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ፣ ትኩረቱና ዒላማው፣ የወያኔን ጎሰኛ ሥርዓት ከነግሳንግሱ ገርስሶ በማስወገድ፣ በሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመተካት እንጅ፣ የወያኔን የፖለቲካ ፕሮግራም ለማሽሞንሞን አይደለም ።

ለመጭው አምስት ዓመት ውል ተፈራርመናልና፣ ውሉ/ኮንትራቱ እስኪያልቅ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ አመፅ ሊመጣ አይችልም የሚለውም ፕሮፓጋንዳ፣ ከምኞትና ከተስፋ የመነጨ የሥነ አእምሮ ዕፎይታ ከመስጠት ያለፈ ፋይዳ አያመጣም። የኮንትራት ስምምነት ለማግኘት፣ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ክፍሎች ተነጋግረውና ተስማምተው የሚፈራረሙት የውል ሰነድ እንጅ፣ አንዱ በብቸኝነት እራሱ አብኩቶ እራሱ የሚጠፈጥፈው አብሽሎ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ጋር የተፈራረመው ውልም ሆነ ኮንትራት የለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ወያኔ ቀጥቅጦ እንዲገዛው ኮንትራት ውል ተፈራርሟል ማለት፣ ሲያንስ የራስን ድንቁርና ባደባባይ

ማውጣት ሲሆን፣ ሲበዛ ደግሞ የአንድን ሕዝብ የአዕምሮ ብስለት መድፈር ይሆናል:: ትዕቢትና ድንቁርና ተዋኀደው የወያኔን ማንነት ከገለፁ ዓመታት ስላለፉ፣ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊያስደንቁ ከቶ አይችሉም:: እንዲያው ለነገሩ፣ የኮንትራት መኖር አለመኖርና፣ በጭቆና ምክንያት ገንፍሎ ከሚመጣ ሕዝባዊ አመፅ ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም:: ጭቆና እስካለ ድረስ አመፅ ይኖራል:: ሕዝባዊ አመፅ ከመጣ ደግሞ የጭቆናን ሥርዓት መዋቅር፣ ዋልታና ማገር፣ መሠረትና ጉልላት በሙሉ ከማፈራረስ ሌላ የቅድሚያ አጀንዳና ተልዕኮ የለውም ::

የወያኔው አለቃ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ አመፅ ሊመጣ አይችልም ለሚለው ማጠየቂያ ያስመዘገበው አራተኛው ነጥብ፣ "ሕዝብ ቅሬታውን ለማሰማት የሚያስችለው ነፃና ግልፅ መድረክ ስለአለው፣ በኢትዮጵያ አመፅ ሊመጣ አይችልም " የሚል ነው:: መቸም እራስን እያታለሉ ለመኖር ልዩ ችሎታን ይጠይቃል ከተባለ፣ በዕርግጥ ይህ ግለሰብ፣ የቤት ሥራውን ሰርቷል ማለት ይቻል ይሆናል:: ግን ሊያምኑት የሚፈልጉትን ነገር ለማመን የቅድሚያ ውሳኔ ማድረግ፣ ችሎታን የሚጠይቅ ክኅሎት ሊሆን አይችልም:: በአምባገነን ገዥዎች አካባቢ የሚያሸረግዱ ግለሰቦች ሁሉ፣ ለአለቆቻቸው የሚያቀብሉት ወሬና መረጃ፣ አለቆቻቸው ሊያዳምጡት የሚያስፈልጋቸውን ሳይሆን፣ ሊሰሙት የሚፈልጉትን ብቻ ስለሆነ፣ ሁልጊዜ አምባገነኖች ራስን እያታለሉ የመኖር ችግር አለባቸው:: በዚህ ሥነ-አዕምሮ ደዌ የተለከፈ ባለሥልጣን፣ እንኳንስ የሀገር መሪ መሆን ቀርቶ፣ ያንድ የመንደር የእግር ኳስ ቡድን አለቃ ሊሆን የሚገባው አይደለም ::

በሀገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተፈራረቁ ገዥዎች ሁሉ ራስን በማታለል ደዌ መለከፋቸው የያዛቸው ልክፍት የሚያጠፋቸው እነርሱን ብቻ ሳይሆን፣ ጠንቁ ለሀገራችንም ጭምር መትረፉ ያሳዝናል:: ደግነቱ ግን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወሰን የሌለው ትዕግስት፣ መሪዎቹ በራሳቸው ድርጊት እስኪጠፉ ድረስ ይታዘባቸዋል እንጅ፣ ከእነርሱ ጋር አብሮ አይከንፍም:: በኢትዮጵያ፣ ሕዝቡ ቅሬታውን የሚገልጽበትና ኃሳቡንም በግልፅ የሚናገርበት ነፃ መድረክ አለውና አመፅ ሊያነሳ አይችልም ብሎ ማለት ከየት የመጣ ድርቅና ነው? ቁጥራቸው በትክክል የማይታወቀው የሀገሪቱ የፖለቲካና የኀሊና እስረኞችና ቤተሰቦቻቸው ይህን ምፀት ሲሰሙ/ቢሰሙ ምን ይሰማቸው ይሆን? የወያኔ ምርጫ 97 ተጭበረበረ ብለው የተቃውሞ ሰልፍ በማድረጋቸው በአደባባይ የተጨፈጨፉት በመቶዎች የሚቆጠሩት ወገኖቻቸን ነፍስ ምን ትል ይሆን? በስድስት ኪሎ፣ በአንዋር መስጊድ፣ በአደባባይ ኢየሱስ፣ በጋምቤላ፣ በኦጋዴንና በሌሎቹም ቦታዎች በግፍ የተረሸኑት ዜጎች ምን በደል ፈጽመው ይሆን? ለእነኝህና ለመሳሰሉት የሕግ፣ የፖለቲካ፣ የታሪክና የኀሊና ጥያቄዎች መላሹ ማን ነው? የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ጥያቄውን እየጠየቀ የሚገባውን መልስም ሆነ ፍትኅ ርትዕ የሚያገኘው በወያኔ ላይ አምፆ በመነሳት በሚጎናፀፈው ነፃ የዳኘነት ሽንጎ እንደሆነ፣ ዛሬ ትዕቢት በተመላበት ምፀት የሚናገሩት የወያኔ መሪዎች ሊገነዘቡት ይገባል:: በአሁኑ ወቅት ግን ነፃ መድረክ የሚባለው ቀልድ የውሃ ሽታ ነው:: ለመሆኑ፣ ነፃ መድረክ ካለ ሕዝብ ሊያምፅ አይችልም የሚል ማታለል ከምን የመጣ ቧልት ነው?

እንደ ሌሎቹ ሀገሮች በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አመፅ ሊነሳ የማይችልበት አምስተኛ የወያኔ ምክንያት፣ በውላቸው መሠረት ተግተው ስለሚሰሩ ነው ተብሏል:: ወያኔዎቹ፣ ይህን ቢሉ ዕውነት አላቸው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂ ጠላቶች መሆናቸውን በተግባር ለመግለፅ በዕርግጥም ተግተው እየሰሩ ናቸው:: አስራ ሰባት ዓመት ተዋግተው ሀገር አስገንጥለዋል:: የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር፣ በቋንቋና በሃይማኖት ለመከፋፈልም ተግተው ሲሠሩ ሲበጠብጡ ቆይተዋል:: የሀገሪቱን ብሔራዊ ሀብት ለግላቸው እያካበቱ ወደ ውጭ በርትተው እያሸሹ ይገኛሉ:: የኢትዮጵያን ለም መሬት ለባዕዳን በመቸብቸብ ትጋታቸውን አሳይተዋል:: ለበላይጠባቂዎቻቸው ትጉህ ታማኝነታቸውን አስመስክረዋል:: ተቃዋሚያቸውን ሁሉ በቻሉበት ገድለዋል፣ አስረዋል፣ አባርረዋል፣ አሰድደዋል:: የሀገሪቱን ምሁራን ደብዛቸውን አጥፍተዋል:: ወጣት ሴቶች ልጆቻችን ወደ የዐረብ ሀገራት ለውርደት ሥራ እንዲጋለጡ ፓስፖርት እያደሉ ልከዋል:: የኢትዮጵያን ድንበር እያስደፈሩ የሀገራችንን መልክዐ- ምድር ጃርት የበላው ዱባ አስመስለውታል:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃነትና ሉዓላዊነት ደፍረው አስደፍረዋል:: ሕዝብን ጨቁኖ ለመግዛት የአምባገነን ሥርዓት ዋናው ዓብነት ሕዝብን ማደኀየትና ማስራብ በመሆኑ ይህንን ዘዴ ወያኔዎች ተጠቅመውበታል:: የኑሮ ዋጋ፣ በየቀኑ ሰማይ-ጠቀስ በመሆኑ ምክንያት፣ ብዙኃኑ የዕለት ጉርስና አስፈላጊ ዕቃዎችን ሊያገኝ አልቻለም:: መሠረታዊ አቅርቦቶች፣ እንደ ቡና፣ ዘይት፣ ስኳር፣ ሽንኩርት፣ በርበሬ፣ ሳሙና፣ ጨውና የመሳሰሉትን ማግኘት እንደ ቅንጦት ተቆጥሯል:: በመሆኑም፣ ወያኔዎቹ፣የኢትዮጵያን ዜጎች፣ አደኀይቶና አስርቦ በመግዛት ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ሥራ ይፈጽማሉ:: ለተራብ ሕዝብ ቂጣ እንጅ ቁጣ አያሻውም በማለት ሳያፍሩ ያሾፋሉ:: ይመፃደቃሉ:: የተግባራቸውን ትጋትና፣የሥራቸውንብርታት ዘርዝሮ የተሟላ ሰንጠረዥ ማቅርብ

ከማይቻልበት ደረጃ መድረሱን የሀገሪቱን ችግር በቅርብ የሚከታተሉ ባለሙያዎች ይናገራሉ ፡፡ ነገር ግን ይህ ሁሉ ብሔራዊ ወንጀል የመሥራት ጥረታቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ አመፅ ገንፍሎ እንዲመጣ ከማደረግ ከቶ አያግደውም፡፡ በመሆኑም፣ የሰሞኑ የወያኔ ፕሮፓጋንዳ የሕዝቡን ልብ ሊማርክና ሊሰልብ አይችልም፡፡ አመፁ የታሪክ ሐቅና ሂደት በመሆኑ አይቀሬ ነውና !

ይህ እያስገመገመ ያለው ሕዝባዊ አመፅ እንዳይነሳና እንዲኮላሽ ወያኔ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ በሀገር ውስጥ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፣ በዓለም ዙሪያ ባለው የኢትዮጵያ (ዲያስፖራ) ኅብረተሰብም ውስጥ ጭምር ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የወያኔ ቀንደኛ ካድሬዎች፣ በአሜሪካ ልዩ ልዩ ከተሞች በመዘዋወር፣ ድጋፍና እርዳታ ለማግኘት እየተሯሯጡ ይገኛሉ፡፡ ለውጥና (ትራንስፈርሜሽንና) ልማት በሚል ሽፋን፣ የስደተኛውን የተቃውሞ ኃይልና ኅብረት ለመሸራረፍ ይሞክራሉ፡፡ ያሁኗን ኢትዮጵያ "አምሳለ-ገነት" ስላደረግናት ሀገራችሁ ግቡና ተጠቃሚዎች ሁኑ በማለት ያሾፋሉ፡፡ የፕሮፓጋንዳቸው ይዘት ይህን ሲመስል፣ በአጣዳፊ ደረጃ የዓላማቸው ትኩረት ግን፣ የሀገር ቤቱ ተቃውሞ ከዲያስፖራው እንቅስቃሴ ጋር እንዳይቀናጅና የአመፁን ሂደት፣ ከተቻለ ለማክሸፍ፣ ያ ካልሆነ ደግሞ አቅጣጫውን እንዲስት ለማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን፣ የሀገር ቤቱና የውጭው የተቀውሞ እንቅስቃሴ ሥር የሰደደና በተለያየ የትግል ሀብል የተያያዘ በመሆኑ የወያኔ ካድሬዎች የሰሞኑ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ብዙም ውጤት እንደማያስገኝላቸው ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡

የአመፁን አቅጣጫ ለማስለወጥና የሕዝቡንም አመፅ ለማኮላሸት ወያኔ እያካሄደ ከሚገኝባቸው ጥረቶች መካከል አንደኛው የውጭ ወራሪ ኃይል የመጣ በማስመሰል የሕዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር መሞከር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ታዲያ፣ የሰሞኑ የወያኔዎች ውጣ ውረድ ብዙም የሚያስገርም ሆኖ አልተገኘም፡፡ ካለፈው ወር ጀምረው በጦር መሣሪያ ግዥ ላይ መረባረብን ቀጥለውበታል፡፡ የመከላከያ ባጀት ጭማሪና በኤርትራ ላይ የጦርነት መሰናዶ የማድረጉ አዝማማያ ሁሉ ሲደመር፣ "ሀገርህ በውጭ ኃይል፣ በጦርነት ልትወረር ስለሆነ ወረራውን ለመከላከል በዝግጅት ላይ ስለምንገኝ፣ ግርግር እንዳታነሳ፡፡ ከሞከርክም ወዮልህ የሚል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠትና በማስፈራራት፣ ከአመፁ ወላፈን የሚድኑበትን የመጀመሪያውን የመከላካያ መስመር ለማስመር እንደሆነ ለማንም ግልፅ ነው፡፡ ይህን ዘዴ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደጋጋሚ ሲሰማ የኖረው ፕሮፓጋንዳ ነው፡፡ የአመፁ ቋያ እንዴት እንዳርበተበታቸው የሚረጋገጠው፣ የወያኔ የመረጃ ቢሮ፣ ሰሞኑን የውጭ ሬዲዮኖችን፣ የኢንተርኔትና ድረ-ገፆችን ሌሎችንም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ መስመሮችን ወደኢትዮጵያ እንዳይተላለፉ ማፈን (ጃም) ማድረጉ ነው፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ሚሊዮን አድማጮች ያሏቸውን እንደ የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ፣ የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ፣ የጀርመን ድምፅ (ዶቼቬለ) ሬዲዮ፣ ... ዓይነቶቹን ፕሮግራማቸው እንዳይሰማ የሚያስተላልፉበትን የአየር ሞገዳቸውን አፍኖታል፡፡ በዐረብ ሀገሮች የተቀሰቀሰውን ሕዝባዊ አመፅ ያቀጣጠለው በብዛት ወጣቱ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባና አካባቢዋ ብቻ ቁጥሩ፣ ወደ አራት መቶ ሽህ (400 000) የሚሆን ወጣት ያለ ሥራ ተቀምጦ መፃዒ ዕድሉን በተስፋና በጉጉት እየተጠባበቀ ይገኛል፡፡ ይህ ትኩስና አምራች ኃይል የሕዝባዊው አመፅ አንድ-አካል አንድ አምሳል መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የለውጡ ፈላጊ ፋና ወጊ ለመሆን የተዘጋጀና ግንባር-ቀደም ሚና ለመጫወት በተጠንቀቅ ላይ በመሆኑ፣ በወያኔ የመረጃና የጥቃት ዒላማ ውስጥ ገብቷል፡፡ ወጣቱና መላው ሕዝብም ይህን በሚገባ ተረድቶ፣ የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ እያደረገ፣ ወያኔ ከሚያደርሰው የአደጋ ጥቃት እራሱን መከላከል ብቻ ሳይሆን፣ አላስፈላጊ መሥዋዕት መክፈል እንደሌለበት ተገንዝቦ፣ የአመፁን መፈንዳት በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡ በኢትዮጵያና በዜጎቿ ላይ የሚፈፀመው ግፍና በደል ሞልቶ እየገነፈለ በመምጣት ላይ ስለሆነ፣ እንደሰደድ እሳት ሲቀጣጠል የሚያቆመው ምድረ- ኃይል ስለማይኖር የየካቲትን 1966 ዓም ሕዝባዊ አመፅን የሚያውቅ ያውቀዋል፡፡

የወያኔ ሹመኞች ግን በወቅቱም በቦታውም ስላልነበሩ፣ ብሎም ለኢትዮጵያ ታሪክና ለዜጎቿ ጥቅም ደንታ ስለሌላቸው ይህን አይገነዘቡትም፡፡ በአሁኑ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንድ የሚያረጋግጠው ሐቅ ቢኖር፣ የወያኔ ሥርዓት ውስጡ እየተፍረከረከ፣ መዋቅሩ እየተቦረቦረ በውስጡ የቀፈቀፋቸው አጋፋሪ ድርጅቶች እየተበወዙ፣ እየተመነጠሩ አመፅ እንዲመጣ ሳይፈጉ አይቀሩም ተብለው የተልጠረጠሩትም እየተያዙ እየተባረሩና ወደ ወህኒ እየተወረወሩ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህ ተጨባጭ ሁኔታ ምንን ያረጋግጣል? በእርግጥ፣ የገዥው ክፍል፣ እርስ በእርሱ እየተጠራጠረና እየተጠባበቀ፣ እየተናቆረና እየተጠላለፈ መምጣቱን የሚያሳይ ምልክትና ማስረጃ ነው፡፡ ሁኔታው እየተባባሰ ሲሄድም፣ "መርከቧ መስጠም ስትጀምር፣ ብልጦቹ እየጣሏት

መዝለል ይጀምራሉ” እንደሚባለው፣ በኢሕአዴግ ዣንጥላ የተጠለሉት የወያኔ ሀረገ-ሬሳ ድርጅቶች ሁሉ ተወግደው፣ ወያኔ ብቻ እንደሚቀር ማንም ሊጠራጠር አይችልም። በመጨረሻም ወያኔ፣ ኢትዮጵያን ማስጠሙ ቀርቶ፣ እርሱ ራሱ እንደሚሰጥም፣ የኢትዮጵያ ታሪክ በተደጋጋሚ መስክሮልናል። የሕዝባዊው አመፅ ቱማታ እየጋለ መጥቶ ወያኔን በሚለበልብበት ወቅት፣ የወያኔ ቀንደኛ መሪዎች ምናልባት፣ “በአልሞት ባይ ተጋዳይነት” ሥነ-አእምሮ ውስጥ በመግባት፣ በግል የሚቆጣጠሩትን የአግዓዚንና የፌዴራል ጦር በመጠቀም በሕዝብ ላይ ጭፍጨፋ ማካሄዳቸው የሚቀር አይሆንም። ቀሪው የመከላካያ ሠራዊት ግን፣ አፈ-ሙዙን ወደ ወገኑ ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማያዞር ተስፋ ይደረጋል። በቀውጢ ቀን፣ ምን ጊዜም ቢሆን የማንኛውም ሀገር የመከላከያ ሠራዊት፣ በመሠረቱ ተልዕኮው የሀገርንና የሕዝብን ደኅንነትና ሠላም ማስጠበቅ በመሆኑ፣ በወገኑ ላይ ጉዳት ለማድረስ ኅሊናው እንደማይፈቅድለት ማስታወስ መንገርም ያስፈልጋል። ሕዝብንና ሀገርን ሲበድሉ የኖሩ ገዥዎች በመጨረሻ ሲጠፉ፣ ዘለዓለማዊቷ ሀገርና ቋሚው ሕዝብ ግን ይኖራሉ። በሀገራችንም አመፅ መምጣቱ የማይቀር ሀቅ ነው። የሕዝብን አመፅ የሚያቆመው አንዳችም ምድራዊ ኃይል የለምና!

ሕዝባዊ አመፅ የሚነሳበትን ትክክለኛ ጊዜና የመጀመሪያውን አቀጣጣይ ምክንያት በቅድሚያ ለመተንበይ አስቸጋሪ ቢሆንም ከሕዝቡ የቁጣ መጠንና ከብሶቱ ደረጃ ስንገመግም በማንኛውም ጊዜ ሊፈነዳ እንደሚችል እንረዳለን። ሕዝቡ አምጾ እምቢተኛነቱን ማሳየት አመፁ የተነሳበት ምክንያት ግቡን ሳይመታ ማለትም የሕዝብ መብት የሚጠበቅበትና ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት የሚሆንበት ሁኔታ ሳይፈጠር በመንገድ ላይ መሰናከል የለበትም። አምባገነኖች ፈሪዎችና ለሰው ልጅ ህይወት ደንታ ስለሌላቸው በተለይ በመጀመሪያ ወቅት በስፋት መግደል በስፋት ማሰር ላይ ይሰማራሉ። የሕዘቡ አመጽ ግቡን ሊመታ የሚችለውና በአመጹ መጀመሪያ ላይ መስዋእትነት የከፈሉት ወገኖች ደማቸው ደመ ከልብ የማይሆው ሕዝቡ ህያው የመንፈስ ጽናትና ቁርጠኛነት ተጎናጽፎ ትግሉን ያለመታከት ሲያፋፍምና ሲያካሂድ ነው።አመጹም የተቀነባበረና የተጠናከረ እንዲሆንም ለሕዝቡ ትክለለኛ አመራርና በመስጠትና አቅጣጫ በማስያዝ በኩል የተደራጁ ኃይሎች ኃላፊነት አለባቸው።

ኢሕአፓ ለዚህ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ታጋዩን ኃይል በማደራጀትና ትግልን የሚያጠናክሩ፣ ተስፋን የሚያለመልሙ፣ አቅጣጫ የሚጠቁሙ መልዕክቶች በሕዝቡ ውስጥ በማሰራጨት ትግሉን በማጠናከር ላይ ይገኛል። ከትግሉ መስክ ለአፍታም ተለይቶ የማያውቀው ኢሕአፓ ሕዝብ የመብቱ ባለቤት የሚሆንበትና፣ ሥልጣን ከሕዝብ የሚፈልቅበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን እስኪሆን ድረስ በተደጋጋሚ የገባውን ቃል ኪዳን በዚህ አጋጣሚም ያድሳል።

በሕዝባዊ አመጽ የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ይደመሰሳል!
ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው!!